የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ዲንካራ ጋዜጣ

AFAR REGION DINKARA GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

ስድስተኛዓመትቁጥር 42
ሠመራ --- የካቲት 22 ቀን 2000 ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት

6th Year No. 42
Samara Feb 30th ,2008

ማውጫ

የቴብር ቀረጥ አዋጅ ..... ገጽ 1

አዋጅ ቁጥር 42/2000

ስለ ቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣ አዋጅ

በሰነዶች ላይ የሚጣለው የቴምብር ቀረጥ የኪነ ጥበብ እድገት፣ የፋይናንስ ተቋሞችን እንቅስቃሴ እና የካፒታል ንብረት ዝውውር ለማገዝ በሚያስችል አኳኋን ማዘጅ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፣

የኢትዮጵያና ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት በጋራ ስብሰባቸው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 99 መሠረት ክልሎች የቀረጥ ቴምብር መወሰንና መሰብሰብ እንደሚችሉ የተወሰነ በመሆኑ፣

በአፋር ብሔራዊ ክለላዊ መንግስት ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ እና ኘ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

አንቀጽ 1

አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልል ስለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል የወጣ አዋጅ ቁጥር 42/2000 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2

ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. ግልግል ማለት ስለ ግልግል፣ ስለ እርቅ፣ ስለስምምነት ወይም ስለ ሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በተደረገ ስምምነት መሠረት በፍ/ቤት ሳይሆን በገላጋዮች አልቆ በጽሁፍ የተሰጠ ውሳኔ ነው፣

2. ማገቻ ማለት የተወሰነ ነገር በመፈፀም ወይም ባለመፈፀም ምክንያት የሚቀር ሆኖ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ ነገር ግን በትዕዛዝ ሆነ ለአምጭው የማይከፈልበት አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውንም ሰነድ ይጨምራል።
3. የህብረት ስምምነት ማለት በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ የሠራተኞች ማህበራት ወኪሎችና በአንድ ወይም ከአንድ በሚበልጡ አሰሪዎች ወይም የአሰሪ ማህበራት ወኪሎች መካከል ስለስራ ሁኔታዎች የሚደረግ በጽሁፍ የሰፈረ ስምምነት ነው።
4. የሥራ ውል ማለት ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ሥራ ለአሰሪው ለመስራት ሲስማሙ በሁለቱ መካከል የሚመሠረት ውል ነው፣
5. ሰነድ ማለት ማናቸውም መብት ወይም ግዴታ የተመሰረተበት፣ የተዘገበበት፣ የተላለፈበት፣ የተወገደበት ልኩ የተወሰነበት ወይም የተሰፋፋበት ወይም የተጠቀሰው ድርጊት ተፈፅሟል የተባለበት ማንኛውም የፅሁፍ መረጃ ነው፣
6. ማረጋገጫ ማለት የህዝብ ጉዳዮችን ለማረጋገጥ ስልጣን ባለው ሰው በሰነዶች ላይ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፣
7. ሰው ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ቢሆንም ባይሆንም ማናቸውም ድርጅት ነው።
8. ሰነድ ማስፈፀም ማለት ሰነድ መስራት፣ ማውጣት፣ በሰነዱ የተመለከተውን ማስፈፀም ወይም ሰነዱን ማዛወር ነው።
9. የመያዣ ሰነድ ማለት ተበዳሪው ወይም ዋሱ ለአበዳሪው በሙሉ ወይም በከፊል ንብረቱን በመያዣነት የሚሰጥበት ሰነድ ነው፣
10. መተዳደሪያ ደንብ እንደአግባብነቱ የመመስረቻ ፅሁፍን ይጨምራል።
11. ክልል ማለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ክልል ነው።
12. የንብረት ባለቤትነትን ማስመዝገቢያ ሰነድ።

አንቀጽ -4

የቀረጡ አተማመን

1. በአንቀጽ 3 ስር በተመለከተው በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ መከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ከዚህ ጋር በመያያዘ በዚህ አዋጅ አካል ሆኖ በሚቆረጠው ሠንጠረዥ ውስጥ እንደተዘረዘረ ይሆናል።
2. አንድ ሰነድ በተደጋጋሚ ተፈፃሚ ሲሆን ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዚሁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው ነው።

አንቀጽ-5

የቀረጡ አተማመን

በአንድ ሰነድ መሰረት ተፈፃሚ ወይም ግዴታ ሊተመን የሚችል ከሆነ በዚሁ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቀረጥ መጠን በሰንጠረዡ ላይ እንደተመለከተው የዋጋው መለቶኛ ይሆናል።

1. በአንድ ሰነድ መሰረት ተፈፃሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የማይል ከሆነ በዚሁ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ለእያንዳንዱ ሰነድ በዚሁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው የቀረጥ መጠን ይሆናል።
2. አንድ ሰነድ ላይ ተከፋይ የሚሆነው ቀረጥ በብር ሳይሆን በለሌላ ገንዘብ ከሆነ የቀረጡ መጠን የሞሰላው ሰነዱ በተገፈፀመበት ቀን በዋለው የምንዛሬ ልክ ነው።
3. በስቶክ ወይም ሌላዋስትና ባለው ነገር ላይ ተመስርቶ ከሆነ በቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈፀመበት ቀን በዋለው አማካኝ ዋጋ መሰረት ነው።
4. ብዙ የተለያዩ ነገሮች የተጠቃለለበት ወይም ለብዙ ልዩ ሰነዶች የቆመ ማናቸውም ሰነድ በያዛቸው ልዩ ልዩ ሰነዶች መጠን በዚህ አዋጅ መሰረት በእያንዳንዱሰነድ ላይ የሚከፈለለው ቀረጥ በመጠቃለል ተደምሮ ይከፈልበታል።
5. ሀ. ንብረት በባለቤትነት ለመማስመዝገብ በተቋቋመ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የሚተመነው በንብረቱ ሰነዱ ውስጥ በተወሰነው የንብረቱ ዋጋ ላይ ሆኖ ዋጋው በቢሮው ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ነው።

   ለ. በንብረቱ ሰነድ ላይ የጠመለከተውን ዋጋ በቢሮው ያልተቀበለው እንደሆነ ተገቢው የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት የንብረቱ ዋጋ ለዚሁ ጉዳይ ቢሮው የሚሰይመው ኮሚቴ ይሰናል።

አንቀጽ 6

የክፍያ ግዴታ

1. ከዚህ በታች በተመለከቱት ንዑስ አንቀፆች በሌላ አከኳኋን ካልተገገለፀ በስተቀር በአንድ ሰነድ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ላይ የሚተመነውን የቴምብር ቀረጥ የሚከፈል ግዴታ አለበት።
2. በክልሉ ውስጥ ሰነዱን ሚሰራው ወይም የሚሰጠው ሰው ሰነዱ እንደተፈፃመ የቴምብር ቀረጡ የመከፈል ግዴታ አለበት።ሆኖም አንድ ሰነድ የተሰራው ወይም የተሰጠው ከክልሉ ውጭ ከሆነ የቴምብር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰነዱን በክልሉ ውስጥ መጀመሪያ ያስፈፀመው ሰው ነው።
3. በኪራይ ውል ውስጥ የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በኪራይ ውል ላይ የሀሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ ያለበት ተከራይ ነው።
4. በመያዣ ሰነድ ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ ተበዳሪው የመክፈል ግዴታ አለበት።

5. በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የሀቴምብር ቀረጥ ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የመክፈል ግዴታ ያለበት የንብረቱ ባለቤትነት የሚመዘገብለት ሰው ይሆናል።
6. ውል ወይም ስምምነት የሀሚመሰረቱ ወገበኖች ለቴምብሩ ቀረጥ በጋራና በተናጠል ተጠገያቂ ይሆናሉ።
7. በቅጥር ውል ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ የአሰሪው ይሆናል።
8. ጉዳያቸውን በግልግል የሚያስወስኑ ወገኖች ለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።
9. በህብረት ስምምነት ላይ ለሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ አሰሪው ሠራተኞች በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ።

አንቀጽ- 7

ቀረጡ የሚከፈልበት ጊዜና ሁኔታ

1. የቴምብር ቀረጥ የሚከፈለው በሚከተለው ጊዜና ሁኔታ ነው።
   ሀ) በመመስረቻና መተዳደሪያ ጽሁፎች ፣ ከምዝገባ በፊት ወይም በምዝገባ ጊዜ
   ለ) በግልግል ውሳኔው ከመሰጠቱ በፊት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ
   ሐ) በውል ወይም በስምምነት ሰነዶች ላይ፤ከመፈረማቸው በፊት ወይም በሚፈርሙበት ጊዜ
   መ) በኪራይ ወይንም በተከራይ አከራይ ውል ላይ ውሉ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ
   ሠ) በማረጋገጫ ሰነድ ላይ፣ ማረጋገጫው በሚሰጥበት ጊዜ
   ረ) በመያዣ ሰነድ ላይ፣ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ
   ሰ) በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ የማስመዝገቡ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም በሚፈፀምበት ጊዜ
   2/ ሀ/ የሚከፈው የቴምብር ቀረጥ ከብር 50 በታች በሚሆንበት ጊዜ ክፍያው ተገቢውን ዋጋ የያዘውን ቴምብር በመለጠፍ ጥፊጽማል።
   ለ/ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር 50 የበለጠ ሲሆን ወይም የሰነዱ ዓይነትና ሁኔታ ለየት ያለ አሠራርን ሲጠይቅ ቢሮው በሚሰጠው መመያ መሠረት ቴምብር ለመለጠፍ በሌላ መንገድ ቀረጡ እነዲከፈል ሊያደርግ ይችላል።
   3/ ሀ/ የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ የሚሰራ ወይም የሚቀበል ሰው በዚህ ቴምብር ሁለተኛ እንዳይሰራ መሠረዝ አለበት
   ለ/ ቴምብር የተለጠፈበትን ሰነድ የሚቀበሉ ሰዎች ስለቴምብሩ አሰራረዝ ቢሮው በሚወስነው መሠረት ይፈጽማሉ።
   ሐ/ በሰነድ ላይ የተለጠፈ ቴምብር በቢሮ በሚወሰነው መሠረት ካልተሰረዘ ሰነዱ ቴምብር እንዳልተለጠፈበት ይቆጠራል።

በዚህ ምክንያት የሚመጣው ኃላፊነት የሚወድቀው በባለጉዳዩ ላይ ሳይሆን የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ በሚሰራ ወይም በሚቀበል ሰው ላይ ይሆናል።

አንቀጽ 8

የቢሮ ስልጣን

ቢሮው የሚኖረው ስልጣን

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰነውን ቀረጥ ለመሰብሰብና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም
2. ቀረጥ ከፋዮች ስለቀረጡ አወሳሰን የሚረዱ፣ መዛግብትና፣ ደብተሮችን፣ ወረቀቶችን፣ ማናቸውም ልዩ ሰነዶችንና ውሳኔዎች እንዲያቀርቡ ለማድረግና ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው እራሱ ቀርቦ እንዲያስመረምር ወይም እንዲያስረዳ ለማዘዝ፣

አንቀጽ 9

ይግባኝ የማቅረብ መብት

ቢሮው በወሰነው የቴምብር ቀረጥ ሂሳብ የማይስማማ ቀረጥ ከፋይ ቢሮው ውሳኔውን በፅሁፍ ካስታወቀበት ቀን አንስቶ ከ 21 ቀኖች በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል።

አንቀጽ 10

የቴምብር ቀረጥ አለመክፈል የሚያስከትለው ውጤት

1. ማንኛውም ሰነድ በዚህ አዋጅ መሠረት ትክክለኛ የቴምብር ቀረጥ ካልተከፈለበት በስተቀር በውል ወይም በሕግ ማስረጃ የመቀበል ስልጣን ባለው ሰው ወይም የመንግስት መስሪያ ቤት ዘንድ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም፣ ምልክት አይደረግበትም ወይም ማረጋገጫ አይሰጥበትም።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው በወንጀል ፍርድ ቤት በሚታይ ክርክር በማስረጃነት የሚቀርቡ ሰነዶች አይመለከትም።
3. በዚህ አዋጅ መሠረት በመረጃነት ተቀባይነት ያላገኙ ሰነዶች ሊከፈልባቸው የሚገባው ቀረጥ በሁለት እጥፍ ተከፍሎባቸው በመረጃነት ሊቀርቡ ይችላሉ። ሆኖም በዚህ ሁኔታ የሚከፈለው ቀረጥ ከቀረጥ ከ 10 ብር ማነስ የለበትም።
4. ከዚህ በላይ በተመለከቱት ንዑስ አንቀጾች የተወሰነው ቅጣት ተፈፃሚ መሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ /12/ መሠረት ከመከሰስ አያግድም።

አንቀጽ 11

ከቀረጥ ነፃ መሆን

1. የቢሮው ኃላፊ በቂ ምክንያት ሲቀርብለት ከቴምብር ቀረጥ ነፃ ሊያደርግ ይችላል።
2. የክልሉ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 7/1991 ተፈፃሚ የሚሆንባቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከቴምብር ቀረጥ ክፍያ ነፃ ናቸው።
3. የአስመጪነት የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸው ነጋዴዎች ለሽያጭ የሚያስመጡት ንብረት በአስመጪዎቹ ስም በሚመዘገብበት ጊዜ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልበትም።
4. መንግስት ባፀደቃቸው ዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች እና ኮንቬንሽኖች መሠረት ሰነዶች ከቴምብር ቀረጥ ነፃ ሊደረጉ ይችላሉ።

5. ተመሳሳይ መበት የተሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ኤምባሲዎችን፣ ቆንሰላዎችን እና ዲኘሎማቲክ ሚሲዮኖችን ሚኒስቴሩ ከቴምብር ቀረጥ ነፃ ሊያደርጋቸው ይችላል።
6. የአክስዮን ድርሻ የምስክር ወረቀት ሲመዘገብ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልም።

አንቀጽ 12

ቅጣት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ በወጣው የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1990 በተደነገገው መሠረት ማንኛውም ሰው፡-

1. ማናቸውንም ቀረጥ ሲከፈልበት የሚገባውን ሰነድ ተገቢው ቴምብር ሳይለጠፍበት ያስፈፀመ ወይም ከምስክርነት በስተቀር የፈረመ እንደሆነ፣
2. ተገቢውን ቀረጥ እንዳይከፍል ለማድረግ በማሰብ የአንድ ሰነድ እውነተኛ ሁኔታ የደበቀ እንደሆነ፣ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 25 ሺህ በማያንስ ከብር 35 ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮና ከ 10 ዓመት በማያንስ ከ 15 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።
3. ከቴምብር ወይም ቴምብር የተለጠፈበት ወረቀት ለመሸጥ ተፈቅዶለት በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን የጣሰ እንደሆነ ወይም
4. ቴምብር ወይም ቴምብር የተለጠፈበት ወረቀት ለመሸጥ ሳይፈቀድለት የሸጠ ወይም ለመሸጥ ያቀረበ እንደሆነ፣ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 5 ሺህ በማያንስና ከብር 20 ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ከ 5 ዓመት በማያንስ ከ 10 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

አንቀጽ 13

ስለመሻር

ማንኛውም ህግ ወይም ልማዳዊ አሰራር ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ 14

ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. ደንብ የማውጣት ስልጣን የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ነው፣
2. ቢሮው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዱ መመሪያዎች ለማውጣት ይችላል

አንቀጽ 15

አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዲንካራ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

የካቲት 22 ቀን 2000 ዓ.ም

እስማኤል አሊ ሲሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር ሠመራ

ተ.ቁ	የሠነዱ ዓይነት	የተወሰደ ስሌት መሰረት	የማስከፈያ ልክ
1	የማንኛውም የንግድ ሥራ ወይም ማናቸው ሌላ ማህበር የተመሰረተበት መተዳደሪያ ደንብ ሀ. መጀመሪያ ሲፈፀም ለ. በመለጠቅ ሲፈፀም	 በቁጥር በቁጥር	 ብር 350 ብር 100
2	የህብረት ሥራ ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ሀ. መጀመሪያ ሲፈፀም ለ. በመለጠቅ ሲፈፀም	 በቁጥር በቁጥር	 ብር 35 ብር 10
3	ግልግል	በዋጋው	የሚተመን 1% የማይተመን ብር 35
4	ማገጃ/ቦርድ/	በዋጋው	1%
5	የእቃ ማከማቻ ማረጋገጫ ሠነድ	በዋጋው	1%
6	ውሎች፣ ስምምነቶችና መግለጫዎቻቸው	በቁጥር	ብር 5
7	የመያዣ ሠነድ	በዋጋው	1%
8	የህብረት ስምምነት ሀ. ሲመዘገብ ለ. ሲሻሻል	 በቁጥር በቁጥር	 ብር 350 ብር 100

9	የቅጥር ውል ስምምነት	የአንድ ወር ደመወዝ	1%
10	ኪራይ፣ ተከራይ አከራይና መሰል መብት ማስተላለፊያ ሠነድ	በዋጋው	0.5%
11	ማረጋገጫ	በቁጥር	ብር 5
12	የውክልና ስልጣን	በቁጥር	ብር 35
13	የንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ	በዋጋው	2%